## የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

# የህብረት ትግል ለድል ዋስትና ነው

በሀገራችን በኢትዮጵያ ላይ የመጣውን መርገም ማለትም የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ በዚህም በዚያም ትግሎች ተካሂደው ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሏል፡፡ ይህ ሁሉ ትግል ግን ብዙ ድሎችን ቢያስመዘግብም፤ የወያኔ አገዛዝ እንዳይረጋጋ ቢያደርግም የመጨረሻ ግቡን መቶ የወያኔን አገዛዝ ሊያስወግድ አልቻለም፡፡ ይህ የሆነበት አንዱ ምክንያት ተቃዋሚ ሀይሎች ሊተባበሩና በጋራ ሊታገሉ ባለመቻላቸው ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

ባለፉት ዓመታት በርካታ የመተባበር ጥረቶች ነበሩ፡፡ ተሳክተው ውጤትን ያስመዘገቡ እንደነበሩት ሁሉ ጀምረው የተደናቀፉ ደግሞ ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ለችግሮቹ የተለያዩ ምክንያቶች የተሰጡ ሲሆን እነዚህን ድክመቶችና ችግሮች ከማስወገዱ አንፃር ግን ድልን መቀዳጀት አለመቻሉ የሚደበቅ አይደለም፡፡ በሁሉም ዘንድ ዋናውን ተልዕኮ አለማስቀደምና ከሁሉም በላይ ሀገርን ለማዳን መረባረቡ ግዳጅ ላይ በገቢር ስምምነት አለመኖሩ በቅድሚያ የሚጠቀስ ነው፡፡ የፖለቲካ ብስለት በማነሱ የተነሳ ሹክቻውና ፉክክሩ ጤናማ አልሆን ብሎ የህብረት ጥረቶችን ጎድቷል፡፡ ለሁሉም ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ዋነኛው ፕሮግራምና ግዳጅ ሀገሪቷን ከጥፋት ማዳንና አንድነቷን በዴሞክራሲ አጅቦ ማረጋገጥ እየሆነ መለስተኛ ፍላጎቶችና ውሱን ዓላማዎች ደንቃራ እየሆኑ ችግር ሲፈጥሩ ቆይተዋል፡፡ ኢሕአፓ በበኩሉ ከድርጅት ውሱን ዓላማ በፊት የጋራውን የሀገርን ማስቀደም ይገባል ሲል የመጀመሪያው አይደለም፡፡

ዛሬ የተቃዋሚ ሀይሎች ሁኔታ የሚያስደስት አለመሆኑ በግልፅ የሚታይ ነው፡፡ ክፍፍሉ ደርቷል፡፡ ይህም በቁጥጥር ስር ሊውል ያልቻለ ሁኔታ ለወያኔ አገዛዝ ሰርጎ ገቦችና ለክፍፍል አራጋቢዎች አመቺ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ባዕዳንም ቢሆኑ ሀገር ወዳድ ሀይሎችን ነጥለው ለማጥቃት የሚረዳቸውን ሁኔታ አግኝተው በመረባረብ ላይ ናቸው፡፡ በአብዛኛው ቅራኔዎቹ መለስተኛና በአግባብ ሊያዙ የሚችሉ መሆናቸው ግልፅ ቢሆንም በተወሰነ ደረጃ ደግሞ ሊታረቁ የማይችሉ ልዩነቶችም መከሰታቸው አልቀረም፡፡ ዛሬ ከወያኔ አገዛዝ ጋር አብሮ መኳዝ ወይስ አገዛዙን ታግሎ መጣል በሚለው ላይ መሰረታዊ ልዩነት ተከስቶ እየታየ ነው፡፡ ይህ ደግሞ መሰረታዊና የሀገርን ህልውናና የነገ ዕጣ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የተሳሳተ አማራጭን የሚገፉትን ሀይሎች መተቸትና ወደ ህዝባዊው መስመር እንዲመጡ መምከሩ ተገቢ ነው፡፡ ኢሕአፓም ከዚህ የተለየ አላደረገም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ተቃዋሚ ሀይሎች ውስጥ የመከፋፈል ሁኔታ ሲታይ በተቻለ መጠን ቅራኔዎች እንዳይካረሩ በመጣር ማርገብና መፍትሄ መሻትን መክሯል፤ በራሱም በድርጅቱ ውስጥ የተከተለውና እየተከተለለ ያለው መንገድ ይህንኑ ነው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ የተቃዋሚ ሀይሎች "ገበና" በአደባባይ ተሰጥቶ ለጠላት እንዳይጠቅም አደራ በማለትና ሀላፊነት በጎደለው መንገድ ወሬ የሚያሰራጩትን በመውቀስ እርምት እንዲደረግ ጥረት አድርጓል፡፡ ከህዝባዊ ጥቅምና መስመር አንፃር ለቀቅተኝነትን ሳያስተናግድ፤ ቅራኔውና ትግሉ ከአገዛዙ ጋር መሆን እንዳለበት እያሳሰበ ቀጠለ እንጂ አንዱን ደግፎ ሌላውን በጅምላ አውግዞ እንዳልሄደ በግልፅ የሚታይ ነው፡፡ ጥቃት ሲደርስበት ቢከላከልም የተሳሳቱ አቅዋሞችን መተቸት--ጉዳዩ የሀገርን ጥቅምና ዕጣ ይመለከታልና-- ግዴታው መሆኑን ደግሞ አልዘነጋም፡፡

---


**EPRP**
**P.O.Box 73337**
**Washington D.C. 20056**
**U.S.A**
**Tel. : (202) 291-4217**
**Fax : (202) 291-7645**

**EPRP**
**BP 22**
**Bois Colombes 92270**
**France**

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com

ተቃዋሚ ሀይሎች በአሁኑ ጊዜ እስከተቻለ ድረስ ክፍፍልን በውይይት አስወግደው በጋራ ሆነው በሀገራችን ጠላት ላይ ሊረባረቡ መጣር አለባቸው:: በዚህ መስክ ኢሕአፓ የእርቅና የህብረት ጥረቱ አጋር እንጂ ተፃራሪ አይደለም:: ልዩነቶች የማይወገዱ ሆነው ከቆዩም በተገቢውና ገንቢ በሆነ መንገድ ይዞና አስተናግዶ ወደፊት ለመጓዝ መጣር ይገባል እንጂ በጠላትነት ደረጃ መተያየቱ ትግልን የሚጎዳ ስህተት ይሆናል:: ከዚህ በተረፈ ግን ኢሕአፓም ሆነ ማንኛውም ሀገር ወዳድ ሀይል ለህዝብ አይጠቅሙም ከሚላቸው አቅዋሞች መራቅ ሆነ መተቸት መብቱ መሆኑ ግልፅ ነው:: በድርጅቶች ውስጥ ጣልቃ መግባት ሌላ፤ ሀገርን የሚጎዳ አቅዋምና ፖለቲካን መተቸት ሌላ:: በዚህ ረገድ ያለውን ልዩነት መረዳት ያሻል:: ለተቀዋሚ ሀይሎች ህብረት እውን መሆን ኢሕአፓ ባለው ተመክሮና ፅናት የበኩሉን አስተዋፅዖ ለማድረግ አይቆጠብም:: በወያኔ አገዛዝ ላይ ድልን ለመቀዳጀት ከህብረት ሌላ መንገድ የለምና::

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!

ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም.

**EPRP**
**P.O.Box 73337**
**Washington D.C. 20056**
**U.S.A**
**Tel. : (202) 291-4217**
**Fax : (202) 291-7645**

**EPRP**
**BP 22**
**Bois Colombes 92270**
**France**

E-mail ESPIC@aol.com Website: http://www.EPRP.com